የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ – የካቲት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 19
ADDIS ABABA– 8th March, 2001

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቍጥር ፸፩/፲፱፻፺፫ ዓ.ም
የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ (ማሻሻያ) ደንብ ........ ገፅ ፩ሺ፬፻፸፪

CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 71/2001
Council of Ministers Financial (Amendment) Regulations ........ Page 1472

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፸፩/፲፱፻፺፫
## የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ (ማሻሻያ) ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፶፯/፲፱፻፹፱ አንቀጽ ፷፰ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፸፩/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር ፲፯/፹፱ (እንደተ ሻሻለ) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል ፤

፩· ከአንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፳፫) ተጨምሯል ፤

"፳፫· "የታከለ ዋጋ" ማለት ከጠቅላላ የማምረቻ ወጪ ላይ ከውጭ አገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሁም ከውጭ አገር ለተገኘ አገል ግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ሲሆን፤ በምርት ላይ የሚከፈሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን አይጨምርም ።

፪· የአንቀጽ ፷፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል ፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 71/2001
## COUNCIL OF MINISTERS FINANCIAL (AMENDMENT) REGULATIONS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995, and Article 68 of the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No. 57/1996.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Council of Ministers Financial (Amendment) Regulations No. 71/2001".

2. *Amendment*

The Council of Ministers Financial Regulations No. 17/96 (as amended) is hereby further amended as follows:

1. The following new Sub-Article (23) is added after Sub-Article (22) of Article 2:

"23) "value added" is the difference between the gross production cost and expenditures made for imported raw materials, other supplies and for services obtained from abroad; but does not include indirect taxes on finished products.

2. Sub-Article (2) of Article 66 is deleted and replaced by the following new sub-Article (2):

"፪. የአገር ውስጥ ምርቶች እና ሥራ ተቋራጮች ከውጭ አገር ምርቶች እና ሥራ ተቋራጮች ጋር ለጨረታ ውድድር በሚቀርቡበት ጊዜ በጨረታ ግምገማ ወቅት ለአገር ውስጥ ምርቶች እና ሥራ ተቋራጮች ልዩ አስተያየት ይደረጋል።"

፫. ከአንቀጽ ፷፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተጨምረዋል ።

"፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለአገር ውስጥ ምርቶች እና ሥራ ተቋራጮች የሚደረገው ልዩ አስተ ያየት ከምክር አገልግሎት በስተቀር ከሥራው ጋር የተያያዘ የትራንስፖርት ፣ የመድን ፣ የተከላ ሥራ ፣ የሥልጠና ፣ የጥገና እና አንድን ፕሮጀክት ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች አገልግሎቶችን ይጨምራል ።"

"፬. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አፈፃፀም፣

፩. ማናቸውም ዕቃ ቢያንስ ከዋጋው ፳ ፐርሰንት (ሃያ በመቶ) በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ ከሆነ የአገር ውስጥ ምርት እንደሆነ ይቆጠራል ። ከዚህ በላይ የተነገረው ቢኖርም የመሠረታዊ ብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ውጤቶች የአገር ውስጥ ምርት እንደሆኑ የሚቆጠረው ከዋጋቸው ፲፭ ፐርሰንት (አሥራ አምስት በመቶ) በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ ሲሆን ነው ።

፪. የገንዘብ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ከተመለከተው በላይ በየምርት ዘርፉ ተፈፃሚ የሚሆነውን መቶኛ በመመሪያ ይወስናል ።"

፬. ከአንቀጽ ፷፷ ንዑስ አንቀጽ ፮ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፯) ፣ (፰) እና (፱) ተጨምረዋል ፤

"፯. ማናቸውም ዕቃ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፷፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው አምራቹ ከዕቃው ዋጋ ቢያንስ ፳ ፐርሰንት (ሃያ በመቶ) እና ከዚያ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ መሆኑን የሚያሳይ በታወቀ ኦዲተር የተረጋገጠ የሂሣብ ሪፖርት ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል ።

፰. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፷፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉ የአገር ውስጥ ምርቶች እና ሥራ ተቋራጮች ከውጭ አገር ምርቶች እና ሥራ ተቋራጮች ጋር ለጨረታ ውድድር በሚቀርቡበት ጊዜ ለውድድሩ አፈፃፀም ሲባል በጨረታ ግምገማ ወቅት በውጭ አገር ምርቶች እና ሥራ ተቋራጮች የመጫረቻ ዋጋ ላይ ፲፭ ፐርሰንት (አሥራ አምስት በመቶ) እንዲ ታከል ይደረጋል ።

፱. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፰) የተደነገገው የአገር ውስጥ ምርቶችን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው ከውጭ አገር ምርቶች ጋር በጥራት ተመሳሳይ ሆነው ሲገኙ ነው ።"

፲. የሥራ ተቋራጮች የልዩ አስተያየቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉበት መመዘኛ እና በዚህ ደንብ የተደነገገው ልዩ አስተያየት በጨረታ ግምገማ ወቅት ተፈፃሚ የሚደረ ግበት ሁኔታ በገንዘብ ሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር



"2) A margin of preference may be granted in the evaluation of bids for goods produced locally and local contractors when comparing them with goods imported from abroad and foreign contractors."

3. The following new Sub-Articles (3) and (4) are added after Sub-Article (2) of Article 66:

"3) Margin of preference given to goods produced locally and local contractors under Sub-Article (1) of this Article shall include expenses for transport, insurance, installation, training, maintenance and other services in connection with the implementation of a project, and directly linked with the good or work, but does not include consultancy services.

4) For the implementation of Sub-Article (2) of this Article,

1) goods shall be deemed to be locally produced if the domestically added value is at least 20%. Notwithstanding the preceding provisions products of metal and engineering industries shall be deemed to be locally produced if the domestically added value is at least 15%;

2) the Minister of Finance shall by directive determine the percentage to be applied for different sectors over and above the percentage indicated under Sub-Article (1) of this Article."

*4. The following new Sub-Article (7), (8), and (9) are added after Sub-Article (6) of Article 66,*

"7) any good shall be eligible for the preference margin under Sub-Article (2) of Article 66 where the producer submits a financial report certified by an independent accountant which shows that domestically added value is at least 20% of the value of the good."

8) for the purpose of evaluation, 15% of the bid price of the imported goods and foreign contractors shall be added on the evaluated bid price of such goods and contractors, when domestically produced goods and local contractors, eligible for the preference margin under Sub-Article (2) of Article 66, are compared with imported goods and foreign contractors.

9) with respect to domestically produced goods the provisions of sub-Article 8 of this Article shall apply only when such goods are of similar quality with imported goods.

10) the eligibility criteria for domestic preference for contractors and the manner in which the preference margin granted under these Regulations is applied shall be detemined by directive issued by the Minister of Finance.

*3. Effective Date*

These Regulations shall come into force as of the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

*Done at Addis Ababa this 8th day of March, 2001.*

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE